# የህሊና ዳኛ

የህሊና ዳኛ ፤ ሞኝን ይሞግተው
መራራውን ትግል ፤ አንጋሎ ይጋተው
ትግሉን ባራዳ አይን ፤ ካልተመለከተው
ቢያሻው እንጦሮንጦስ ፤ ገሃነም ይከተተው ።

ለኔ አልተስማማኝም ፤ አክራሪው በሞላ
አገር አገር ይላል ፤ ሞኝ ነው ተላላ
ዘረኛን ሲያወግዝ ፤ ከገንጣይ ሲጣላ
ወያኔን ይጋፋል ፤ ተኝቶ እንዳይበላ
ወይ ሰርቆ አይበላ ፤ ወይ ሌላ አያስበላ
እሱ እየተጎዳ ፤ ለሕዝብ እያደላ
ትግል ትግል ይላል ፤ ሆዱን እንዳይሞላ
ተግባር ምን ይሰራል ፤ አፍ ነው የሚያበላ ።

ከስጦታ ሁሉ ፤ አምላክ አድሎኝ
ምላሴን ሰንጥቆ ፤ ሁለት አርጎልኝ
ከህሊና ይልቅ ፤ ሆዴ በልጦልኝ
ተግባሬን ደብቆ ፤ አፌ አሹሎልኝ
ልቤ ወደ ነዋይ ፤ ሄዶ አስደሰተኝ ።

ከግራም ከቀኝም ፤ በዝቶ ማባበሉ
ሳትወጣ ሳትወርድ ፤ ዘርፈው የሚያበሉ
መደመር መቀነስ ፤ ሂሳብ የሚያሰሉ
ብሩን በጆንያ ፤ ፊቴ ሲቆልሉ
አፍና ተግባሬ ፤ አልጣጣም አሉ ።

ዛሬም እንደ ትላንት ፤ መጣሁኝ ዳግመኛ
ለወያኔ ልቆም ፤ ጠባቂ ዘበኛ
ሥም እያጠፋሁኝ ፤ እያልኩ ቂመኛ
ለገንዘብ ለስልጣን ፤ ተሸነፍኩ ከፋኛ
በፍቅሩ ተይዤ ፤ ሆኛለሁ ምርኮኛ
አንዴ ካመለጠ ፤ አይመጣም ዳግመኛ
አጉል ከመጨነቅ ፤ በህሊና ዳኛ
የለቱን በልቼ ፤ ጠግቤ ልተኛ ።

የህሊና ዳኛ ፤ አይሞግተኝ ከቶ
አስተኝቼዋለሁ ፤ አልብሼ ዲሪቶ
ገበታ ዋንጫዬ ፤ ጢም ብሎ ሞልቶ
ሁሉን አገኛለሁ ፤ ተመስገን ምን ጠፍቶ

ለደሃና ላገር ፤ ማስብ ትላንት ቀርቶ
ህሊናና ደሃ ፤ ይኑር ተጎልቶ
ትግል ላይ ሲያላዝን ፤ ይቀራል ተረስቶ ።

ከህሊና ዳኛ ፤ ሙግትም አልሻ
ቢያነሳ ቢጥለኝ ፤ ምን ጎድቶኝ አበሻ
ደንታም አይሰጠኝም ፤ ንቅሻና ውቅሻ
ላነሳ ሄጃለሁ ፤ እኔም የኔን ድርሻ
መቼም አልመለስ ፤ እስከ መጨረሻ ።

የህሊና ዳኛ ፤ ላያስር ላይፈታ
እንዴት ትቼ ልሂድ ፤ ያማረ እፍታ
መዳራት መጨፈር ፤መዝፈንና እስክስታ
ትግል ትግል እያልኩ ፤ አልረግጥም ገበታ ።

ታዛቢው